Amharic

# በምውአለ ህጻን ስለመጀመር- ትክክለኛው ጊዜ መቼ ነው?



ህጻናት ት/ቤት ለመጀመር አንድ ዓመት ሲቀራቸው ወደ ምውአለ ህጻን እንዲሄዱ በቪክቶሪያ መንግሥት በኩል የገንዘብ እርዳታ ይቀርባል። .

ህጻናት ለመማር ዝግጁ ሲሆኑ በመደበኛ ት/ቤት ውስጥ እንዲጀምሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ህጻናት ወደ ምውአለ ህጻን የሚሄዱበት ትክክለኛ ጊዜ በወላጆች እንደሚወሰነው ሁሉ - እንዲሁም ወላጆች ልጃቸውን ት/ቤት ለማስጀመር ትክክለኛውን ጊዜ ግምት ውስጥ ማስገባቱ አስፈላጊ ነው።

- ወላጆች ልጃቸው በሚቀጥለው ዓመት ት/ቤት ላለመጀመር ከወሰኑ፤ በምውአለ ህጻን ፕሮግራም የጀመረ ማንኛውም ህጻን ማቋረጥ ይችል ይሆናል። ብዙጊዜ ከዚህ ውሳኔ ላይ የሚደረሰው በወላጆችና በምውአለ ህጻኑ አስተማሪ መካከል ስለ ህጻኑ ፍላጎት በተመለከተ ውይይት ከተደረገ በኋላ ነው። የተርም 2 ከማለቁ በፊት ከምውአለ ህጻኑ ፕሮግራም ልጃቸው የሚወጣ ከሆነ፣ አሁንም ለሚቀጥለው ዓመት ማለት ህጻኑ ት/ቤት ከመጀመሩ በፊት ለአንድ ዓመት የሚሆን ወደ ምውአለ ህጻኑ መመለስ ይችላል።
- ህጻናት “የእድገት ዝግመት” እንዳለባቸው ከታወቀ በሁለተኛው ዓመት የምውአለ ህጻናት እድል ይሰጣል (‘ልጄ በሁለተኛው ዓመት የምውአለ ህጻን ያስፈልገዋልን?’ የሚለውን ፅሁፍ ማየት)።

ወላጆች ልጃቸው በምውአለ ህጻን ፕሮግራም ከመሄዳቸው በፊት ሌላ ዓመት ስለመጠበቅ ጥቅም የማማረጫ መረጃ ሲቀርብላቸው ሊደናገሩ ይችላሉ። እባክዎ ለአገልግሎት አቅራቢ ሠራተኛ ያነጋግሩ።

## ለምውአለ ህጻን ሌላ ዓመት ስለመጠበቅ

የልጅዎ እድሜ በምውአለ ህጻን ለመጀመር እንዲቻል አስተዋየ ቢኖረውም፣ እያንዳንዱ ህጻን የራሱ/የራሷ የሆነ እድገት ደረጃ ሊኖረ/ራት ይችል ይሆናል፣ በተጨማሪም ልጅዎ ይህንን ልምድ ለማግኘትና ለምውአለ ህጻን ተመክሮ ዝግጁ እንዳይሆን የሚያስቸግሩ ሌሎች ነገሮች ሊያድርበት/ባት ይችላል።

ልጅዎ ምውአለ ህጻን እንዲጀምር ከወሰኑና ከጀመረ፣ እርስዎና አስተማሪው ልጅዎ ለዚህ ተሞክሮ ስግጁ ስላለመሆን ምልክት ለማየት ይችሉ ይሆናል። ከመጀመሪያው በርስዎና በአስተማሪው መካከል ግልጽነት ሲያስፈልግ፣ ይህም በርስዎና በአስተማሪው መካከል ቅንነት የተሞላበት ግንኙነት በመፍጠር፣ የህጻኑን ፍላጎትና የቤተሰቡን ፍላጎት ለማሟላት ቅድሚያ መስጠት ይሆናል።

ልጅዎ ለአንድ ዓመት ከጠበቀ/ች የሚያሳየው ለምውአለ ህጻኑ ተሞክሮ ከጊዜው ጋር በበለጠ ጥቅም ለማግኘት ማዳበር እንደሚቻል ነው። ብዙጊዜ ከህጻኑ የአእምሮ ብስለት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ሲሆን፣ ታዲያ በዚህ ሁኔታ ላይ ልጅዎ በተርም 2 መጨረሻ ላይ የምውአለ ህጻናቱን ከለቀቀ/ች ከጊዜ በኋላ የሚጠፋ ጉዳይ ይሆናል። ከዚያም በሚቀጥለው ዓመት የሙሉ ዓመት ምውአለ ህጻን እድል ማግኘት ይችላል/ትችላለች።

ማንኛውም ወላጅ በተርም 2 መጨረሻ ላይ ልጁን በማስወጣት ለምውአለ ህጻኑ የተመደበውን የዓመት ጊዜ ህጻኑ በቀጣዩ ዓመት እንዲመለስበት ማድረግ ይቻላል።

## ያስተውሉ

- ልጅዎ በምውአለ ህጻን መቼ መለማመድ እንዳለበት በጥንቃቄ ማሰብና ትክክለኛ ጊዜን መለየት ይሆናል። እርግጠኛ ካልሆኑ ልጅዎን ለሚያውቁ ሌሎች ሰዎችና ጥሩ ግምት ይሰጣሉ ብለው ለሚያምኗቸው ሰዎች ማነጋገር።
- ወደ ምውአለ ህጻን በመሄድ ወይም በመረጃ አቅርቦት ትምህርት ላይ በመገኘት ስለምውአለ ህጻን ፕሮግራም መጠየቅ።
- ልጅዎ በምውአለ ህጻን ፕሮግራም ከመጀመሩ/ሯ በፊትና በኋላ ስለልጅዎ ያለዎትን ሃሳብና አሳሳቢ ጉዳይ በግልጽ ከአስተማሪ ጋር መነጋገር።
- ልጅዎ በምውአለ ህጻን ለመግባት ስለትክክለኛ ጊዜ በተመለከተ በበለጠ ማብራሪያ ወይም መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ ለህጻኑ አስተማሪ፣ ለህጻን እንክብካቤ አስተባባሪ ወይም ለእናቶችና ህጻን ጤና ጠባቂ ነርስ ያነጋግሩ።

በቪክቶሪያ መንግሥት አነሳሽነት የተጀመረ

© የትምህርትና የመጀመሪያ የልጅነት ጊዜ እድገት መምሪያ፣ 2007 ዓ.ም